# የአብክመ ፍ/ቤቶች ዕጩ ዳኞች ምልመላ ሥርዓት አፈጻጸም መመሪያ

በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 69/1994 ዓ.ም አንቀጽ 6 /1/ /ለ/ እና 20 በተሰጠ ስልጣን መሠረት ይህ የክልሉ እጩ ዳኞች ምልመላ ሥርዓት አፈጻጸም መመሪያ በክልሉ የዳኞች አስተዳደር አብይ ጉባኤ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የአብክመ ፍ/ቤቶች የዕጩ ዳኞች ምልመላ ሥርዓት ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2004 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጉም

በዚህ መመሪያ ውስጥ፤-

1. “ምክር ቤት” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልል ም/ቤት ነው፡፡
2. “ጉባኤ” ማለት በአዋጅ ቁጥር 64/1994 ዓ.ም መሠረት የተቋቋመው የክልሉ የዳኞች አስተዳደር አብይ ጉባኤ ነው፡፡
3. “ዳኛ” ማለት በክልሉ ፍ/ቤቶች በዳኝነት እንዲያገለግል በም/ቤቱ የሚሾም ማለት ነው፡፡
4. “ኮሚቴ” ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት ለክልሉ ፍ/ቤቶች እጩ ዳኞችን ለመመልመል በጉባኤው የሚቋቋም ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው፡፡
5. “ምልመላ” ማለት ለክልሉ ፍ/ቤቶች ለዳኝነት አወዳድሮ እና እንደ አስፈላጊነቱ አሠልጥኖ በጉባኤው በኩል ለምክር ቤቱ ለሹመት እንዲቀርቡ የማድረግ ሂደት ነው፡፡
6. “ዕጩ” ማለት የምልመላውን ሂደት አልፎ በጉባኤው አቅራቢነት ለምክር ቤቱ ለሹመት የሚቀርብ ግለሠብ ነው፡፡
7. “የዞን ጉባኤ” ማለት በአዋጅ ቁጥር 64/1994 ዓ.ም መሠረት በብሔረሰብ ወይም በዞን አስተዳደር ደረጃ የተቋቋመ የዳኞች አስተደደር ንዑስ ጉባኤ ነው፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ በየደረጃው በሚገኙ የአብክመ ፍ/ቤቶች የሚሾሙ እጩ ዳኞችን መልምሎ ለሹመት እስከ ማቅረብ ያለው የአሠራር ስርዓት የሚመራበት ነው፡፡

2. ጉባኤዉ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘዉ በክልሉ ዉስጥ ለሚገኙ የብሄረሰብ ዞኖች የዕጩ ዳኞች ምልመላን በተመለከተ በከፊልም ሆነ በሙሉ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ እንዳይሆን ሊወስን ይችላል፡፡

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በክልሉ ፍ/ቤቶች የሚሾሙ ዳኞች አሿሿም ግልጽነት በሠፈነበት እና ተዓማኒ በሆነ ስርዓት በመምራት የላቀ ሙያዊና ሥነ ምግባራዊ ብቃት ያላቸው ዕጩ ዳኞች ለሹመት መቅረባቸውን ማረጋገጥ እና እጩ ዳኞች ለሹመት የሚቀርቡት ግልፅ ማስታወቂያ ወጥቶ በውድድር እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

## 5. የጉብኤው ሥልጣንና ተግባር

በዚህ መመሪያ እና በሌሎች ህጎች የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤዉ

1. የክልሉ ዕጩ ዳኞች ምልመላ ስርዓት በበላይነት ይከታተላል
2. የጉባኤው ሰብሳቢ የዳኞች ምልመላ ኮሚቴን መቋቋም አስመልክቶ የሚያቀርበውን መነሻ ሀሳብ ይመረምራል፤ የኮሚቴውን መቋቋም ይወስናል፡፡
3. ለዳኝነት ሥራ የሚወጡ ማስታወቂያዎችና ለተወዳዳሪዎች ማሠራጫ መንገዶችን እንዲሁም የመመዘኛ ነጥቦች ይዘት ይወስናል፡፡
4. ለተወዳዳሪዎች የተዘጋጁ የጽሑፍ ፈተናዎችን ይገመግማል፡፡
5. በጊዜያዊ ኮሚቴው የሚቀርብለትን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሠጣል፡፡
6. የተሻለ ውጤት አግኝተው ለእጩነት ብቁ መሆናቸው የተረጋገጠ ተወዳዳሪዎች ለሹመት እንዲቀርቡ ውሳኔ ይሠጣል፡፡
7. እንደ አስፈላጊነቱ የምልመላ ስርዓቱ በዞን ጉባኤ እንዲፈፀም ውክልና ይሠጣል፡፡

## 6. የምልመላ ጊዜያዊ ኮሚቴ አወቃቀር

1. ጉባኤው በማንኛውም የምልመላ ደረጃ በእጩ ዳኞች ምልመላ ሒደት ኃላፊነቶች ተሠጥተውት የሚሠራ ጊዜያዊ ኮሚቴ ሊያቋቁም ወይም በዞን ጉባኤ እንዲቋቋም ሊወስን ይችላል፡፡
2. የኮሚቴው አባላት በጉባኤው ሠብሳቢ አቅራቢነት በጉባኤው ይመረጣሉ፡፡
3. ኮሚቴው ከሶስት እስከ አምስት አባላት ይኖሩታል፡፡
4. የኮሚቴው ሊቀመንበርና ፀሐፊ በጉባኤው ይመረጣሉ፡፡
5. ኮሚቴው ውሳኔዎችን በሙሉ ድምጽ ማሳለፍ ካልቻለ የአብላጫው ድምጽ ውሳኔ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 7. የጊዜያዊ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር

1. ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸውን አመልካቾች ይመዘግባል፤ እንደአስፈላጊነቱ ውክልና በመስጠት እንዲመዘገቡ ሊያደርግ ይችላል፤ አጠቃላይ የምልመላ ሂደቱን ያስተባብራል፣ ምልመላው ስለደረሰበት ሁኔታ በየጊዜው ለጉባኤው ሠብሣቢ ሪፖርት ያቀርባል::

2. ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡትን ማስረጃ ከአስገዳጅ መስፈርቶች አንጻር ያጣራል፡፡
3. በተወዳዳሪዎች የቀረቡ ማስረጃዎችን ያደራጃል፣ በጠቅላይ ፍ/ቤቱ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት እንዲቀመጡ ያደርጋል፣ በጉባኤው በተጠየቀ ጊዜ ያቀርባል፡፡
4. የጽሑፍ ፈተና ዝግጅት እና እርማት ያደርጋል፣ አጠቃላይ ዉጤት ይሰጣል፤ ስለ አፈጻጸሙም ለጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል፡፡
5. የፈተና ውጤቶችን በተመለከተ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይቀበላል፣ ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 8. ዓመታዊ የሠው ኃይል ፍላጎት ዕቅድ

1. ክፍት ለሆኑ ወይም አዲስ ለሚፈጠሩ የዳኝነት ቦታዎች እጩዎች የሚመለመሉት ጉባኤው በየአመቱ መጀመሪያ የሚያጸድቀውን የሠው ኃይል እቅድ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
2. የጉባኤው ሰብሳቢ የፍ/ቤቶችን የዳኛ አቅርቦት ፍላጎት እያየ አስፈላጊ የሆኑት ዳኞች እንዲመለመሉ ለጉባኤው ጥያቄ ያቀርባል፡፡
3. ጉባኤውም እንደቀረበለት ጥያቄ አንገብጋቢነት መዝኖ ግዜያዊ ኮሚቴ እንዲዋቀር እና የተወዳዳሪዎች ምዝገባ እንዲጀመር ያዛል፡፡

## 9. ተፈላጊ መመዘኛዎች

1. በዚህ መመሪያ የተመለከቱ አስገዳጅ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉባኤው ለዳኝነት የሚጠየቁትን ተፈላጊ የምልመላ መመዘኛዎች በጉባኤው ሰብሳቢ አቅራቢነት መርምሮ ይወስናል፡፡
2. የፀደቀው ተፈላጊ መመዘኛ ለኮሚቴው እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

### 10. ተወዳዳሪዎችን መጋበዝ

1. ለዳኝነት ሥራ የሚወጡ ማስታወቂያዎች በጉባዔው ተዘጋጅተው በኮሚቴው እንደየአግባብነቱ በፍ/ቤቶች ማስታወቂያ ሠሌዳ፣ በሌሎች ሠፊ ስርጭት ባላቸው የህትመት ውጤቶች፣ በኤሌክትሮኒክ መረጃ ማሠራጫዎች እና ሌሎች መረጃ ማሠራጫዎች ይፋ ይደረጋሉ፡፡
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጉባኤው የውስጥ ማስታወቂያ እንዲወጣ ሊያዝ ወይም በግል ተወዳዳሪዎችን ሊጋብዝ ይችላል፡፡

### 11.<u>የማስታወቂያ ይዘት</u>

የዳኝነት ሥራ ማስታወቂያ ቢያንስ፡-

- የፍ/ቤቱን ደረጃ፣
- ዝቅተኛ መመዘኛዎችን፤
- መቅረብ የሚገባቸውን ማስረጃዎች፣

- ተፈላጊ የሠው ኃይል ብዛት እና፣
- ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የያዘ ይሆናል፡፡

12. <u>ማስታወቂያ ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ እና ምዝገባ</u>
    1. ለማንኛውም የክልሉ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥራ የሚወጣው ማስታወቂያ ጉባኤው በሚያዝዘው መሠረት ለሚወሰን ጊዜ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡
    2. ማስታወቂያው ክፍት ሆኖ በሚቆይባቸው ተከታታይ ቀናት በተቻለ መጠን ለአመልካቾች አመቺ በሆኑ አማራጭ መንገዶች ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘዉን የሥራ መጠየቂያ ቅፅ "፩" እንዲሞሉና አስፈላጊ መረጃዎቻቸውን እንዲያያይዙ ይደረጋል፡፡
    3. መመዝገቢያ ቦታና ተጨማሪ የመመዝገቢያ መንገዶች በግዜያዊ ኮሚቴዉ የሚመቻቹ ሆኖ ኮሚቴዉ ምዝገባውን በአካል ወይም በቴክኖሎጂ ውጤቶች ግብዓትነት በማካሔድ የተወዳዳሪዎችን የተሟላ ማመልከቻ አሠባስቦ ያጣራል፣ አደራጅቶ ያስቀምጣል/ዶኩመንት ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መስፈርቶችና ምዘና

### ንዑስ ክፍል አንድ - አስገዳጅ መስፈርቶች

13. <u>የትምህርት ደረጃ</u>
    1. ለማንኛውም ፍ/ቤት እጩ ዳኝነት ምልመላ ብቁ ለመሆን ማንኛውም ተወዳዳሪ ቢያንስ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ሊኖረው ይገባል፡፡
    2. ከዚህ በላይ በንዑስ ቁጥር '1' የተጠቀሠው የትምህርት ደረጃ ዝቅተኛውን መመዘኛ የሚያመለክት ሲሆን እንደሚፈለገው የተወዳዳሪዎች ብዛት እየታየ የተሻለ ውጤት እንዲሁም የትምህርት ደረጃ ያላቸው ተወዳዳሪዎች ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

14. **የስራ ልምድ/ ስልጠና**
    1. **ለወረዳ ፍ/ቤት**

       በፍትህ አካላት ማሰልጠኛ ማዕከል በሚሰጠዉ የቅድመ ዕጩነት ስልጠና ያለፈ እና ለዳኝነት የተደለደለ ለወረዳ ፍርድ ቤት ዳኝነት ለሹመት ይቀርባል፡፡
    2. **ለዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**

       በወረዳ ፍ/ቤት በዳኝነት ስራ ላይ ያሉ፤ እንዲሁም በየትኛዉም ደረጃ ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት በሬጅስትራርነት፤ በህግ ኦፊሰርነት እና በተከላካይ ጠበቃነት በማገልገል ላይ ያሉ ለዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እጩ ዳኝነት ለመወዳደር ***የሶስት ዓመት*** የሥራ ልምድ እንደ ዝቅተኛ ልምድ ይታሠባል፡፡

3. **ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት**

በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት ስራ ላይ ያለ፤ እንዲሁም በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ከዚያ በላይ ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት በሬጅስትራርነት፤ በህግ ኦፊሰርነት እና በተከላካይ ጠበቃነት በማገልገል ላይ ያለ፤ ለክልል ጠ/ፍ/ቤት በእጩ ዳኝነት ለመወዳደር ባለበት ፍ/ቤት ***የአራት ዓመት*** የሥራ ልምድ እንደ ዝቅተኛ ልምድ ይታሠባል፡፡

4. በህግ ሁለተኛ ድግሪ እና ከዚያም በላይ ያላቸዉ አመልካቾች ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም እንደ ***ሁለት ዓመት*** የሥራ ልምድ ይያዛል፡፡

15. **አስገዳጅ መስፈርቶች ስለመሆናቸዉ**

1. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የትምህርት እና ሥራ ልምድ መስፈርቶች አንድ ተወዳዳሪ ለውድድር ለመቅረብ የግድ ማሟላት የሚገባውን ዝቅተኛ መመዘኛ የሚያሳዮ በመሆናቸው ወደ ጎን ሊደረጉ አይችሉም።
2. ከዚህ በላይ ባለው ንዑስ ቁጥር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠቀሱትን አነስተኛ መስፈርቶች በርካታ ተወዳዳሪዎች የሚያሟሉ ሲሆን በምልመላ ወቅት እንደሚፈለገው የተወዳዳሪዎች ብዛት እየታየ የተሻለ የትምህርት ዉጤት ያላቸው ተወዳዳሪዎች ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል።
3. አንድ ዓይነት የሥራ ልምድ እና የትምህርት ዉጤት ባላቸው ተወዳዳሪዎች መካከል መምረጥ አስፈላጊ ሲሆን ለሙያው ቅርበት ያለዉ ተወዳዳሪ ቅድሚያ ሊሠጠው ይችላል።

16. **ምክንያታዊ ልዩነት**

ከዚህ በላይ ባሉት ቁጥሮች የተነገሩት እንደተጠበቁ ሆነው በአስገዳጅ መስፈርቶቹ በተወዳዳሪዎች መካከል ተመጣጣኝ የምዘና ውጤት ሲኖር የሴቶችንና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ለማሳደግ ሲባል ለነዚህ ተወዳዳሪዎች ቅድሚያ ሊሠጥ ይችላል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት - ፈተና

17. **የፈተናዉ ይዘትና አላማ**

1) የክልሉ ፍ/ቤቶች እጩ ዳኞችን በመመልመሉ ሒደት ለተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ ፈተናዎች እና መመዘኛዎች ይዘት ተወዳዳሪዎች ለዳኝነት ሙያ አስፈላጊ የሆነውን እውቀት፣ ታታሪነት፣ ሥነምግባር፣ ፍትሃዊነት፣ ሕግ አክባሪነት ፣ መልካም ስም እንዲሁም ሌሎች ተገቢ ሁኔታዎችን የሚያሟሉ መሆኑን በቀጥታ የሚመዝን ሊሆን ይገባል።
2) ከዚህ በላይ ባለው ንዑስ ክፍል ባሉት አናቅጽ የተዘረዘሩትን አስገዳጅ መስፈርቶች ማጣሪያ ላለፉ ተወዳዳሪዎች ፈተና ይሠጣል።

## 18. የፈተናዉ አይነት

1) ተወዳዳሪዎችን ለመመዘን የፅሁፍ ወይም የቃል ፈተና ወይም ሁለቱም ዓይነት ፈተና ሊሠጥ ይችላል፡፡
2) እንዲሁም በጉባኤዉ ዉሳኔ ተወዳዳሪዎች ፈተና የሚያካትት የአጭር ጊዜ ስልጠና እንዲወስዱ ሊደረግ የችላል፡፡

## 19. የፈተናዉ አፈጻጸም

የፈተና ዝግጅትና እርማት በዋነኝነት የግዜያዊ ኮሚቴዉ ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ቢሆንም የሚዘጋጁት ፈተናዎች እና ለተወዳዳሪዎች የሚሠጠው ውጤት በጉባኤው ሊፀደቅ ይገባል፡፡

## 20. የስራ ዓፈጻጸም ምዘና

1. ጉባኤው በሌላ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ለእጩ ዳኝነት የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት ይመዘናሉ፡፡
2. በሬጅስትራርነት፣ በህግ ኦፊሰርነት እና በተከላካይ ጠበቃነት በማገልገል ላይ ያሉ አመልካቾች የስራ አፈጻጸም ምዘና ከዳኞች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 21. የጽሁፍ ፈተና

1. የጽሁፍ ፈተና ዝርዝር ይዘትና ነጥብ አያያዝ ፈተናውን በሚያወጣው አካል የሚወሰን ቢሆንም በአጠቃላይ ግን ፈተናው ቢያንስ ተወዳዳሪዎች በየጊዜው ክርክር በሚነሳባቸው ህጎች ፣በስነ ስርዓት ህጎች፣ በህግ አጻጻፍ እና ትንተና (legal writing and reasoning) ረገድ ያላቸውን ብቃት የሚመዝን ሆኖ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ነገርግን ጉባኤው የጽሁፍ ፈተናውን ገምግሞ እንደ አስፈላጊነቱ እንዲስተካከል ማዘዝ ይችላል፡፡
2. ጉባኤው በሌላ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ለእጩ ዳኝነት የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎች በጉባኤው በሚመረጡ ፈተናውን ለማዘጋጀት ብቃት ባላቸው የህግ ባለሙያዎች እንደየአግባብነቱ ተዘጋጅቶ የሚታረም የጽሁፍ ፈተና እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡
3. ፈተናውን ያዘጋጀው አካል በፈተናው ቀን ፈታኝ (Invigilator) ሆኖ ሊመደብ አይችልም፡፡ የጉባኤው ሰብሳቢ ሌሎች ፈታኞች እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡
4. ፈታኞች ለተወዳዳሪዎች የሚስጥር ቁጥር ወይም ኮድ እንዲኖራቸው በማድረግ ስለሚስጥራዊነቱ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡

## 22. የፈተና ውጤት

1. ለተወዳዳሪዎች የሚሰጡ ፈተናዎች የሚይዙት አጠቃላይ ነጥብ 100% ሲሆን ከዚህም ውስጥ ጉባኤው በሌላ ሁኔታ ካልወሠነ በቀር የስራ አፈጻጸም ምዘና 25% ፡ የጽሁፍ ፈተናው ደግሞ 75% ይይዛል፡፡
2. በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉ ቢኖርም ለስራ አፈጻጸም ምዘና ኮሚቴዉ ማጣራት አድርጎ የሚሰጠው ውጤት ዝርዝር ስሌቱ በዚህ መመሪያ አባሪ "፪" የተመለከተዉ ሆኖ የተያዘዉ 25% ነጥብ በሚከተለዉ ይተካል
   - ለስራ አፈጻጸም (የውሳኔ ጥራት፤ ብዛት፤……) - 15%
   - መልካም ስነምግባር - 2.5%
   - አገልግሎት አሰጣጥ - 2.5%
   - ለለዉጥ ያለዉ ተነሳሽነት - 2.5%
   - ለመሀደር ጥራት 2.5%
3. በዚህ ደረጃ በአጠቃላይ ውጤታቸው ከሌሎች ተወዳዳሪዎች የተሻሉ ተወዳዳሪዎች ***በጊዜያዊነት ለቅድመ እጩነት*** ብቁ እንደሆኑ ተቆጥሮ በአጭር ግዜ ዉስጥ ውጤታቸውን እንዲያውቁ እንደየአግባብነቱ በጉባኤው ምርጫ በማስታወቂያ ሠሌዳ፣ በሌሎች ሠፊ ስርጭት ባላቸው የህትመት ውጤቶች፣ በኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ወይም በሌላ መንገድ ይፋ ሊደረግ ይችላል፡፡

## 23. ቅሬታ አቀራረብ

1. የፈተና ምዘና ውጤት ስህተት አለ በሚል የሚቀርቡ ቅሬታዎች በሊቀመንበሩ በኩል ለኮሚቴው ይቀርባሉ፡፡
2. ቅሬታው የፈተና ውጤት ከተገለፀበት አንስቶ ባሉት አምስት የሥራ ቀናት ሊቀርብ ይገባል፡፡
3. ኮሚቴው የቀረበለትን ቅሬታ የተባለው ስህተት ሊመለከተው ከሚችል አካል ጋር በመመካከር አጣርቶ በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው ውሳኔ ይሠጣል፡፡
4. በስራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ላይ ቅሬታ ሲቀርብ የአጻጻፍ ወይም የስሌት ስህተት ካልኖረበት በስተቀር ሊቀየር ወይም ሊስተካከል አይችልም ፡፡
5. በኮሚቴው በሚሠጠው ውሳኔ ያልተስማማ ተወዳዳሪ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለጉባኤው ሠብሣቢ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
6. በኮሚቴው የተደረገ የውጤት ማስተካከያ ጉባኤው ካላፀደቀው በቀር ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

24. የተወዳዳሪዎች ምዘና የመጨረሻ ውጤት

1. ከመቶ በሚገኘው አጠቃላይ ውጤት የተሻለ ውጤት አግኝተው ለእጩነት ብቁ መሆናቸው በጉባኤው የተረጋገጠ ተወዳዳሪዎች ጉባኤው በሚወስነው መንገድ ውጤታቸው እንዲገለፅላቸው ይደረጋል፡፡
2. የጉባኤዉ ሰብሳቢ ዉጤቱ ከመገለጹ በፊት በፈተናዉ የተሻለ ውጤት አግኝተው ለእጩነት ብቁ መሆናቸው የተረጋገጠ ተወዳዳሪዎች ላይ ህዝብን ከሚወክሉ ባለድርሻ አካላት አስተያየት ይቀበላል፡፡ ያገኘዉን አስተያየት ከፈተናው ውጤት ጋር አካቶ ለጉባኤው ያቀርባል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

25. መመሪያውን ስለማሻሻል

የክልሉ የዳኞች አስተዳደር አብይ ጉባኤ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘዉ ይህንን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

26. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

የኔነህ ስመኝ

የአ/ብ/ክ/መ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ

ሠብሣቢ

## <u>አባሪ ፩</u>

## <u>ለአብክመ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት የማመልከቻ ቅፅ</u>

1. <u>የአመልካች የግል ሁኔታ</u>

1.1 ሙሉ ስም ከነአያት

______________________________ ________________________ _________________________

1.2 የትውልድ ዘመን

ቀን __________ ወር ______________ዓ.ም________

1.3 የአሁኑ የመኖሪያ አድራሻ

አገር _________ ከተማ ___________ ክ/ከተማ ___________ ቀበሌ ____________

1.4 ፆታ ☐ ሴት ☐ ወንድ

1.5 ዜግነት ________________________

1.6 ብሔር _________________________

1.7 ዕድሜ _________________________

1.8 የቤተሰብ ሁኔታ ☐ ያገባ ☐ ያላገባ

1.9 ቋንቋ፡ በቂ፣ ጥሩ፣ በጣም ጥሩ እና እጅግ በጣም ጥሩ በሚል ይገለፅ፡፡

| ቋንቋ | መናገር | መስማት | መፃፍ | ማንበብ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

2. <u>የአመልካች የትምህርት ደረጃ መግለጫ</u>

| | የትምህርት ቤቱ/ተቋሙ ስም | የተማሩበት ጊዜ<br>ከ - እስከ | ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1ኛ ደረጃ ትምህርት | | | |
| 2ኛ ደረጃ ትምህርት | | | |
| የመጀመሪያ ድግሪ | | | |
| ሁለተኛ ዲግሪ | | | |
| ዶክትሬት ዲግሪ | | | |

3. <u>የአመልካች የስራ ልምድ</u>

| የመሥሪያ ቤቱ ሥም | የሠሩበት ጊዜ ከ - እስከ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ሥራውን የለቀቁበት ምክንያት |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |

4. <u>የሙያ ሥልጠና ተሳትፎ ካሎት ይጥቀሱ</u>

| ሥልጠናውን የወሰዱበት ተቋም ስም | የስልጠናው ርዕስ | ሥልጠናው የወሰደው ጊዜ<br>ከ - እስከ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

ከዚህ በላይ ያቀረብኩት መግለጫ እውነትና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

**የአመልካች ስምና ፊርማ** **ቀን፣ ወርና ዓ.ም**

________________________ ________________________

